## ምዕራፍ አራት

## 4. የስደተኞች መንደር (አዱሉም)

### የእግዚአብሔር ራእይ ያለው ትውልድና ፈተናው

‹‹ያዕቆብም ለፈርዖን አለው፡- የእንግድነቱ ዘመን መቶ ሰላሳ ዓመት ነው፤ የሕይወቴ ዘመኖች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ፥ አባቶቼ በእንግድነት የተቀመጡበትንም ዘመን አያህሉም፡፡›› ዘፍጥ.47÷9

በዚህች ዓለም ላይ ፈተናዎች ጎልተው የሚመጡት፤ በምድራዊው ኑሮዋችን፣ በሀብታችንና በእውቀታችን ላይ ብቻ አይደለም፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች ያለውን ራእይ የሚጻረር መንገዳችንን ተከታትሎ የሚያጠቃን፤ መነሻችንንና መድረሻችንን፣ ሥራችንንና ታሪካችንን ለማጥፋትና እንዲሁም ለማበላሸት፤ ብሎም አቅጣጫዎችን ለመለወጥ የሚተጋ መንፈስ እንዳለ፤ ብዙዎቻችን ገና አልተረዳነውም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ክፉ መንፈስ በጣም ትልቁና ብርቱ ጥንቃቄ የሚያደርገው፤ የእግዚአብሔር ራእይ ወደ እግዚአብሔር ሰው እንዳይወርድና ወደ ሕዝቡም፤ እንዳደርስ ማገድና መከልከል ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ አብርሃም ብዙ መንገዶችን ተጉዟል፡፡ የእግዚአብሔርን ራእይ ለመጠበቅ ወይም ደግሞ ወደ ራእዩ ለመድረስ ሲባል የሚመጣውን ፈተና በብዙ መንገድ ተቋቁሞ አልፎታል፡፡

አብርሃም ጠላት በተነሳበት ወቅት፤ እግዚአብሔር አምላክ ጠላቶቹን ሀሳባቸውን በማስለወጥ፤ እንዲሸልሙት አደርጓል፡፡

ሰይጣን፤ ረሃብ ባመጣበት ዘመን፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን የተስፋውንና የቃል ኪዳኑን ኃይል ለማዛባትና በዕድሉም እንዲያማርር ለማድረግ፤ ብዙ ዘመቻ አድርጎበት የነበረ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር አምላክ የረሃቡን ጊዜ ሽሮና ለውጦ፤ በምድረ በዳ ውስጥ የከበረና ታላቅ ባለሃብት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ዘፍ.12፡10





ከዚህ በተጨማሪም፤ እግዚአብሔር አምላክ ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል ኪዳኑ፤ ለዘሮቹና ለልጅ ልጆቹ እንደሚሰጥ ተናግሯል፡፡ ይህንን የሰማው ዲያብሎስም፤ የአብርሃምን ዘር ለማጥፋት ያላደረገው ጥረት አልነበረም፡፡

ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ወለደ፡፡ ከአስራ ሁለቱ ልጆቹ አንደኛው <u>ይሁዳ</u>፤ አባቱ በተለይ ራእይ ያየለት ሰው ነው፡፡ የይሁዳ ራእይ በእግዚአብሔርና በያዕቆብ መካከል የሚያልፍ ነው፡፡ አባቶች ራእያቸውን ለማያዩ አድርገው ወደ ትውልዱ ማስተላለፍ ካልቻሉ በራሱ ችግር ነው፡፡

### የእግዚአብሔር ራእይ በይሁዳ ሕይወት ውስጥ

### 4.1 የይሁዳ እናት ልያ

ልያ የምታባለው የራሔል እህት፤ ለያዕቆብ ደግ፣ ቅን፣ የዋህ፣ ንጹህ የፍቅር ሴት ሆና ተገኝታለች፡፡ ይሁን እንጂ፤ እግዚአብሔር ከልያ ጋር ነበር፡፡ ስሟ፤ ዓይኗ ትንሽ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ <u>ልያ</u> ማለት <u>ዓይነ-ደካማ፤ ዓይነ ሞጭሟጫ</u> ማለት ነው፡፡ <u>ራሔል</u> ማለት ደግሞ፤ <u>እንደ ቄብ በግ የምትዘል ዓይነ ፈጣጣ</u> ማለት ነው፡፡

ሚስቱን የማይወደውና በሚስቱ ውበት ያልተማረከው ያዕቆብ፤ ለልያ ብዙ ትኩረት ባይሰጣትም፤ ውበት የማያየውና በመልክ የማይመዝነው እግዚአብሔር ግን፤ ከልያ ጋር ነበር፡፡

ኑሮዋ ሁሉ ብዙ ፈተና የበዛበት በመሆኑ፤ ለወለደቻቸው ልጆች ሁሉ ያወጣችው ስም፤ በቤትዋ ውስጥ ያለውን መከራና በያዕቆብ ላይ ያለውን ተለዋዋጭ ጠባይና ገጽታ የሚመለከት ነበር፡፡

እንደማንኛውም ሰው ኑሮዋን የያዘችው ቢሆንም፤ በጣም የተቸገረችበት ግን፤ በቤተሰቡ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት አለመኖር እንዲሁም፤ እርሷ በበጎ ሁኔታ አለመታየትዋ ነበር፡፡

ርስቱ የሆነ፤ ሌላ ተጨማሪ ርስት የሌለው፤ ዘወትር አምላኩን ርስት አድርጎ የሚኖር ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ፤ በመንፈሳዊ የክህነት አገልግሎት አባት የሚባል፤ ለዘለዓለም በደህንነት ጸጋ ውስጥ በዕጣኑ መስዋዕት በኩል <u>ጸሎት የሚያሳርግ</u> ካህን ነው።

ዲያብሎስ ከሚያካሂዳቸው ትላልቅ ዘመቻዎች መካከል አንዱ፤ መጀመሪያ መጠጊያ እንድታጣ ማድረግ ነው። ከአንተ ጉልበት፣ ሕይወት፣ ጠባይ፤ ቤተሰብ ወጥቶ፤ መጠጊያ የሚከለክሉህ ብዙዎች ናቸው።

አንተን መስለውና አህለው እንዳንተ ተምረው፤ መጠጊያ ለማሳጣት የሚታገሉ ጥቂቶች አይደሉም። በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም መንገድ ከልያ የሕይወት ቋንቋ ውስጥ ክብደት ያለው አንዱ ቃል <u>‹‹መጠጊያ አገኘሁ››</u> የሚለው ነው።

በቢሮአችን መጠጊያ ያገኘን ሰዎች ስንት ነን? ተሸማቀን በፍርሃት እንኖራለን። የፍርሃት ደመወዝ እንቀበላለን። የፍርሃት እንጀራ እንበላለን።

በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩል፤ መጠጊያ ያገኘነው የቱ ጋር ነው? መከራ እያየን፣ ስቃይ ውስጥ ገብተን፣ እየፈራን፣ እየተጠራጠርን፣ እየደነገጥንና እየተጨነቅን ነው የምንጠጋው? ልያ ግን በትክክለኛው የሕይወት ራእይ መጠጊያ አገኘሁ ነው ያለችው።

የመከራ ሃሳቦችና የመከራ ሕሊናዎች፤ ሁልጊዜ የሚያስገኙት ውጤት፤ የተዘበራረቀ እንደሚሆን ከልያ የመጀመሪያ ልጅ ከሮቤል ሕይወት እንገነዘባለን።

ከዚህ በኋላ አራተኛ ልጅ ጸነሰች። ወንድ ልጅም ወለደች። ስሙንም ‹‹ <u>ይሁዳ</u> ›› ብላ ጠራችው። ይሁዳ ማለት <u>‹‹እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ</u>›› ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ልያ በጸና የእምነት ታሪክ ውስጥ ለማለፍ ልዩና ታላቅ ዕድል አገኘች።





ልያ መውለድ ያቆመችው <u>በምሥጋና ልጅ</u> ላይ ነው። በመሆኑም፤ ለይሁዳ ይህ የእናቱ የምስጋና ራእይ በወደፊት ሕይወቱ ውስጥ እየተከተለው የሚገለጥ ይሆናል ማለት ነው።

ይሁዳ አደገ፤ ጎለመሰ፤ ኃይል አገኘ፤ ጠነከረ፤ ከሌሎች ወንድሞቹ በተሻለ መንገድ በግርማ ሞገሱ ተገለጠ።

ከዚያ በኋላ አባቱ ያዕቆብ የሚቀጥለውን ራእይ ለልጁ ለይሁዳ ማየት ጀመረ።

እግዚአብሔር የሚወደው፤ ለስሙ በምስጋና የተጠራ፤ ለክብሩ የተመረጠ፤ ለኃይሉ መገለጫ የሚሆን፣ ከልቧ ከሕይወቷና ከማሕጸኗ ጀምሮ ለማያዊ ፍቅር ያልተለያት፤ ብስጭት፣ ንዴት፣ ሁከት ከውስጧ በራቀ ጊዜ የተጸነሰና የተወለደ ልጅ በመሆኑ፤ <u>እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ</u> በማለት ጊዜውንና ዘመኑን ለእግዚአብሔር ምስጋና ሰጠች። የእምነት ትክሻዋም፤ በእግዚአብሔር የምስጋና ኃይል ላይ አረፈ።

ይሁዳ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ስም በመሆኑ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዲያብሎስ በቅናት <u>በይሁዳ ላይ መሸመቅ</u> ጀመረ። ልዩ ልዩ ዓይነት ፈተናዎች የሚመጡበትና ውስብስብ ችግሮች የሚጋለጡበት ሰው ሆነ።

ይህ እንግዲህ በእናቱ በኩል ያለውን ራእይ የሚቃወመውና የሚፋለመው ክፉ መንፈስ፤ ከእርሱ ጎን እየተንቀሳቀሰ ዕለት ከዕለት ውጊያን ከፈተበት።

እናትዬው በጥላቻ ማዕበል ውስጥ እንደተሰቃየች ሁሉ ይሁዳም፤ በትላልቅ የክፋትና የተንኮል ሴራዎችን በሚያከናውኑ ዘሮች ተከቦ፤ የክፉ ዓለም መንፈስ ውጊያ ውስጥ እንዲኖርና እግዚአብሔርን እንዲዘነጋ፤ <u>ዲያብሎስ ይከተለው</u> ጀመር።

ከዚያ በፊት ግን የአባቱ የያዕቆብ ራዕይ ለይሁዳ ምን ነበር? ዘፍ. 49፥1 ላይ እንዲህ ይላል። ‹‹ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ

ላሳረፈልህ ለእግዚአብሔር ነው፡፡ የተስፋው የቃል ኪዳን ኃይል በአንተ በኩል ስለሚገለጽ፤ የአባቶችህ ልጆች ለአንተ ይሰግዳሉ አለው፡፡

የዛሬው መናፍቅ ግን፤ እኔ ለቅዱሳንና ለጻድቃን አልሰግድም የሚለው፤ <u>ልቡ ውስጥ ዲያብሎስ</u> ስላለ ነው፡፡ እዚህ ላይ የአባቶችህ ልጆች፤ የመጣው ትውልድ ሁሉ ለአንተ ይሰግዳል ያለው እግዚአብሔር ነው፡፡ ለእርሱ የተንበረከኩ ሁሉ ከእግዚአብሔር በረከት ይቀበላሉ፤ ይካፈላሉ፡፡

**እንደሴት አንበሳ አደባ ይላል ቀጥሎ፤** በዚህ በያዕቆብ የይሁዳ ተስፋ ውስጥ ዓመተ ፍዳዎች ሲያበቁ <u>ቅድስት ድንግል ማርያም</u> ተጸነሰች፤ ተወለደች፡፡ «**አሸናፊው አንበሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወለደ፡፡**» ሉቃ. 1÷26

እግዚአብሔር ለያዕቆብ ባሳየው ራእይ ውስጥ ለፍቅርና ለሞገስ እናት የምትሆን በይሁዳ ሕይወት ውስጥ አተኩሮ ተመለከተ፡፡

ዛሬ በእኛ ሕይወት ግን፤ በአባቶቻችን እጅ ትውልድን የሚያሳይ ራእይ ስለሌለ፤ ምንጊዜም የዲያብሎስ ተጠቂዎች ነን፡፡

አቅጣጫን የሚያሳይ ራእይ የለንም፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትን ዘንግተን ራእዮቻችን የሚመነጩት ከምድራዊ ፍልስፍና ውስጥ ስለሆነ፤ ተሰናክለናል፡፡

ሌላው ደግሞ፤ «**እንደ ሴት አንበሳ አደባ፤ ያስነሳው ዘንድ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፣ ገዥ ሆኖ እስኪመጣ ድረስ፤ የሕዝብ መታዘዝ ለእርሱ ይሆናል፡፡ ውርንጫውን በወይን ግንድ ላይ ያስራል**» ዘፍ. 49÷10-11 ይላል፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አስራ አምስት ላይ እንዲህ ይላል፡፡ «**እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡**» ብሏል፡፡ ዮሐ. 15÷5





የያዕቆብ ራእይ ለአራተኛው ልጁ ለይሁዳ ያየው፤ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ «**ውርንጫውን በወይን ግንድ ላይ ያስራል፡፡ የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ**» ከዚያም ቀጥሎ «**ልብሱን በወይን ያጥባል**» ይላል፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እዚህ ዓለም መጥቶ፤ <u>ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ፤ የዘላለም ሕይወት አለው</u>፤ ሲል ተናግሮአል፡፡ ደሙን የሰጠው በወይኑ በኩል ሲሆን ሥጋውን ደግሞ፤ በስንዴው በኩል ሰጠን፡፡

ያዕቆብ፤ **ለይሁዳ መጎናጸፊያውንም በወይን ደም** ያለው፤ ምን ታይቶት ነው? አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን በገረፉትና በጦር በወጉት ጊዜ፤ መጎናጸፊያው በደም ተነከረ፡፡ ስለዚህ ያዕቆብ የይሁዳን ራእይ ሲያይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስንም እየተመለከተው ነበር፡፡

የአብርሃም የተስፋ ራእይ በያዕቆብ በኩል ዘመን ሳይሽረው፤ ገና አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት ማብቂያው ላይ፤ የሚሆነውንና የሚወለደውን፤ በይሁዳ ልጆች መካከል የሚገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን በይሁዳ በኩል አይቶታል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያሰቃዩት እምባውን ያፈስ ነበር፡፡ እምባ የሚፈስበት ዓይን ደግሞ ይቀላል፡፡ «**ጥርሱ ከወተት ይልቅ ነጭ ይሆናል**» ይላል፡፡ ደም የሚፈሳትን አንዲት ሴት ከኋላው ስትዳስሰው ፈገግ ብሎ፤ «**ማነው የዳሰሰኝ?**» አለ፡፡ ሴቲቱም በፈገግታው ነጫጭ ጥርሶቹን ስታይ፤ የፍቅር ድምጽ መሆኑ ስለገባት፤ «**እኔ ነኝ፤ የነካሁህ**» አለች፡፡ እርሱም «**ሂጂ! እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ግቢ**» አላት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፤ «**አባት ሆይ የሚሰሩትን አያውቃምና፤ ይቀር በላቸው**» ሲልም፤ ነጭ ጥርሱን እያሳየ ነበር፡፡ በጦር እየተወጋም፤ <u>**ይቅርታን**</u> ያስተምር ነበር፡፡ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙ እየፈሰሰ ቂም ያልያዘ፤ ሁልጊዜ ፈገግ ያለ፤ ቤዛችንንና

መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ያዕቆብ በይሁዳ ራዕይ ውስጥ አይቶታል።

**<u>የይሁዳ ራእይ ቅደም ተከተል፤</u>**

ሀ. የእናቱ፤

ለ. የአባቱ፤

ሐ. የሙሴ፤

መ. የዳዊት፤

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን፤ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁሉ እንደ ይሁዳ የሚከታተለው መሆኑን ነው። ይኼውም የእግዚአብሔር ራእይ ፀሌላቸው ዓለማውያን ሰዎች ዘንድ፤ የሰይጣን ጥቃት በተለየ መንገድ ነው። ምክንያቱም፤ አንዴ በቁጥጥሩ ሥር ከማዋሉ ጋራ ተያይዞ፤ የሚፈጽማቸው ተግባሮች እግዚአብሔርን ከሚፈልጉትና፤ እግዚአብሔርን ከሚያምኑት ፈተናው እኩል አይደለም።

ሐሳቡና ተግባሩን የሚያከናውኑለት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የክፋትና የጣዖት አምልኮት ጠባይ ስለሚገልጥባቸውና የእግዚአብሔርን የመኖር ክብር፤ ሞገስ፣ ጸጋ፣ ቸርነቱንና ደህንነቱን ከሕይወታቸው እንዲርቅ በማድረግ፤ የክፉ ሥራው መግለጫና ማንጸባረቂያ ስለሚያደርጋቸው፤ ለሌላው ፈታኝ እንዲሆኑ በተለያየ ጥፋትና ተንኮል ላይ እንዲሰማሩ ለክፉው መንፈስ ግብር የግፍ አቅጣጫን የሚከተሉ ትውልዶች ለመሆናቸው እንደምሳሌ የምንጠቅሰው በሙሴ ዘመን የነበሩትን የሞአብን ነገድ ነው።

የሞአብ ነገድ በእርግማን ሥራና በሟርት አምልኮት የሚታወቅ ስለሆነ፤ <u>በለዓም</u> የሚባል ረጋሚ፤ የሞአብ መንግሥት የቅርብ አማካሪና ባለሟል እንደነበረ በዘኁልቁ ከምዕራፍ 21 እስከ ምዕራፍ 23 ድረስ መመልከት ይቻላል።



በማለዳ መያ'ዝ

በእርግማን መንፈስ የእስራኤልን ሕዝብ ለማዳከምና መንገዱን ለማሳት የተነሳው በለዓም፤ አነሳሱ ከምን አንጻር እንደሆነ ስንገነዘበው በክፋት ዘሮች በኩል ዲያብሎስ ሠራተኛ ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

‹‹እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ!›› እና ‹‹በእንተ-ማርያም መሐረነ ክርስቶስ›› የሚለውን ትውልደ ክርስቲያን፤ ራእይ፣ ሃይማኖት፤ ጸሎትና ምግባር ያለውን፤ በተለያየ ችግርና መከራ ይፈታተነዋል።

ምክንያቱም ራእይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዲያብሎስ ይሁዳን እንደተከተለው ይከታተልሃል።

ክብሩንና ጸጋውን፣ ቸርነቱንና ማዳኑን፣ በረከትና ተስፋውን ከሕልውናህ ወጥቶ እንድትረሳውና እንድትዘነጋው፤ ችላ እንድትለው፤ በሃይማኖትና በሥነ-ምግባር እንደተራቆቱት አሕዛብ ዓይነት ሰዎች እንድትሆንለት መልካም አስተሳሰብህ እንዲመክን፤ እንድትባዝን፤ ራእይህ እንዲበላሽ ዲያብሎስ ይከታተልሃል።

**<u>በሙሴ ዘመን ይሁዳ፤</u>**

**ዘዳግም 33፥1-7 ላይ ‹‹ የእግዘአብሔር ሰው ሙሴ ሳይሞት የእስራኤልን ልጆች የባረከባት በረከት ይህች ናት። ........የይሁዳ በረከት ይህ ነው፤ እንዲህም አለ፦ አቤቱ፣ የይሁዳን ድምጽ ስማ፣ ወደ ወገኖቹም አግባው፤ እጆቹም ይጠንክሩለት፤ በጠላቶቹ ላይ ረዳት ትሆነዋለህ››።** ይላል።

እንግዲህ ስለ ይሁዳ እንዲህ ዓይነት ራእይ ነበር። ከቤተሰቡ ራእይ ያላየ ትውልድ ይንኮታኮታል። የሚመጣበትን ሁኔታ ያልነገሩት ትውልድ፤ የሚጠብቀው እግዚአብሔር ሳይሆን፤ ለማጥፋትና ለማውደም፤ ወቅትና ጊዜ የሚጠብቅው የክፉው መንፈስ አገዛዝና ምሪት ነው። በሰው ሀሳብና በአሕዛብ ምክር የሚመራ ተፈጥሮ ላይ የሚወድቅ ይሆናል። ይሁዳ ግን፤ ከእናቱ ከአባቱ፤ ከሙሴና ከዳዊት የአኗኗር መንፈሳዊ ታሪኩና በእምነቱ ውስጥ ባለው ተስፋ፤ ራእዩ ተገልጿል።

## <u>የዳዊት ራእይ ስለ ይሁዳ</u>

በመዝሙረ ዳዊት 75(76) ፥1-2 ላይ «ተአውቀ፤ እግዚአብሔር በይሁዳ » ይላል፡፡ እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፡፡ ማለት ነው፡፡ « ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው፡፡ ሥፍራው በሳሌም፣ ማደሪያውም በጽዮን ነው፡፡» አለ፡፡ ጽዮን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ሳሌም ማለት ደግሞ፤ የሰላም ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሲከናወን ዲያብሎስ ይሰማል፤ ይቀናል፡፡ የይሁዳን በረከት ለማስቀረትና ለማበላሸት ይከታተለዋል፡፡

የይሁዳ ራእዩ ተስፋ፣ ቃል ኪዳን ያለው የዘር ቅድስና የቤተሰብ ሕልውናው ከልዑል አምላክ ፍቅርና ሞገስ ጋር የተሳሰረ ስለነበር፤ ዲያብሎስ ያሳድደው ጀምሯል፡፡

... ዳዊት ይሁዳን ሲያየው « **እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፡፡**» ብሎ ከመሰከረ በኋላ ቀጠለ፤ « **በዚያም የቀስትን ኃይል፣ ጋሻን ሰይፍን ሰልፍንም ሰበረ፤ በዚያም ቀንዶችን ሰበረ፡፡ አንተ በዘላለም ተራሮች ሆነህ በድንቅ ታበራለህ፡፡ ልበ ሰነፎች ሁሉ ደነገጡ፤ እንቅልፋቸውንም አንቀላፉ፤ ባለጠጎች ሁሉ በእነርሱ እጅ ምንም አላገኙም፡፡ የያዕቆብ አምላክ ሆይ፣ ከተግሣጽህ የተነሣ ፈረሰኞች ሁሉ አንቀላፉ፡፡ አንተ ግን፣ አንተ ግሩም ነህ፡፡ ቁጣህን ማን ይቃወማል?** » ይላል፡፡ ዳዊት በመዝሙሩ፡፡ መዝ.75 (76) ፥1-7

## <u>የይሁዳ ፈተና፤</u>

ብዙ ጊዜ ዲያብሎስ ራእይ ያለውን ትውልድ ለማጥቃት በቀዳሚነት ይንቀሳቀሳል፡፡ <u>አባቶች የጸለዩለትን</u> ትውልድ ሌላውን እንዳይጠቅም፤ የመከራ ልጆችን ከጎኑ አስቀምጦ ለሌሎች ፈተና እንዲሆን ለማድረግ ይሰለፋል፡፡

በዚሁ መሠረት፤ እነዚህን የፈተና ልጆች፤ ከቤተሰቡ፤ ከጎረቤቱና ከአካባቢ አስቀምጦ፤ በዘመድና በጓደኛ በኩል የሚያመጣው





ችግር የተወሳሰበ ከመሆኑም በላይ፤ የክፋት ሥራውን ማንቀሳቀሻ በማድረግ ይጠቀምባቸዋል፡፡

ዲያብሎስ የተባረከ ተግባር እንዳይኖር፤ የተቀደሰው ተቀድሶ እንዳይኖር፤ በበረከት የቆመው በበረከት እንዳይኖር፤ የሚያውቀው ያለአዋቂ እንዲሆን፤ የተማረው እንዲጠፋበት፤ ያገኘው እንዲያጣ፤ የለበሰው እንዲራቆት፤ የሞቀው እንዲበርደው፤ ዕድሉ የተቃናለት እንዲዘጋበት፣ የሚበላው እንዳይጠረቃ፣ የጠጣው እንዳይረካ፣ ሁልጊዜ ትግል ላይ ያለ መንፈስ ነው፡፡

ይህ የተለመደው <u>የዚህ ዓለም ገዢ የዲያብሎስ መንፈስ አንዱ ትልቁ ሥራውና የጥፋት ተልዕኮው ነው፡፡</u>

ስለዚህ የተባረከው ትውልድ የቀዘቀዘና ሞራሉ የደከመ እንዲሆን ከሚከፍተው ዘመቻዎች መካከል አንዳንዶቹን በይሁዳ ሕይወት ውስጥ እንመለከታለን፡፡

**«በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ ወረደ፡፡»** ይላል፡፡ **ዘፍጥ 38፥1** በዚህ ቃል ውስጥ ሁለት ከበድ ያሉ ቃላትን እናያለን፡፡ አንደኛው <u>ተለየ</u>፤ ሁለተኛው ደግሞ <u>ወረደ</u>፡፡

## <u>መለየት</u>

መለየት በአሉታዊነት፤ ዛሬ በእኛም ሕይወት ውስጥ የብዙዎቻችን መለያ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የተለየ ሀሳብ፣ የተለየ አመለካከት፣ የተለየ አቅጣጫ፤ የተለየ ዕቅድ፤ የተለየ ቋንቋ፤ የተለየ ባሕርይ አላቸው የምንላቸው ሰዎች ዛሬ ይበዛሉ፡፡

መለየት በእያንዳንዱ ሕይወት ጠባይ ውስጥ ሲከሰትና ሲታይ፤ ሰዎች ይጨነቃሉ፤ ተስፋቸውም ይመናመናል፡፡ አእምሯቸው ከልበናቸው ይጣላል፡፡ በዚህ ጊዜ ከሌላው ሰው ጋር መግባባት ይሳናቸዋል፡፡ ይህ የመለየት ጠባይ አካልና ውጤት፤ የመናፍስቱ አንዱ መገለጫ መንገድ ነው፡፡

<u>ተለይቶ መቆም፤</u>

በአንድ ወቅት ከአባቶቻችን እምነት፣ ባሕልና ልማድ ርቀን ለብቻችን ቆምን:: በፈጠርነው በእዚህ የራሳችን ዓለም ውስጥ፤ ግማሹን የኛ፤ ቀሪውን ደግሞ የውጭ ትምህርትን አንድ ላይ አድርገን ወደፊት ለመራመድ ሞከርን::

ለየት እያልን በሄድን ቁጥር፤ አባቶቻችን ዲያብሎስን ድል የነሱበትና ያሸነፉበትን፤ ጠላትን የሰበሩበትን መንገድ፤ ስውሩን የክፉ መናፍስትን ውጊያ ጠንቅቀው ያወቁበትን መንፈሳዊ ኃይልና አቅጣጫ እየተውነውና እየራቅነው፤ ለጸሎትና ለምስጋና እየሰለቸንና እየደከምን ስንመጣ፤ ያለን ብቸኛ አማራጭ እንደ ይሁዳ መለየት ነው::

የጸሎቱን፣ የጾሙንና የስግደቱን፣ የንጹህ አምልኮትን መንፈሳዊ ሕይወት ትተን፤ የምስጋናውንና ቅድሰናውን በረከቱን ችላ ባልን ቁጥር፤ የጸሎት መጽሐፎቻችን ቋንቋ እንኳን አልጥም ብሎን፤ በምትኩ የራሳችንን የተለየ ዘዴና ዘመናዊ የአስተሳሰብ ፍልስፍና ለመያዝ ሞከርን:: <u>ግን አልሆነም:: ለምን? ከእግዚአብሔር ተለይተናልና</u>! ዮሐ፤15÷5 ላይ ‹‹ ያለእኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና ›› ይላል::

ይሁዳ ከተጠቃበት አንዱና ዋናው መንገድ፤ <u>ከእውነተኛው መንገድ ተለይቶ መውረዱ</u> ነው:: ይሁዳን ብቻ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትልቅ አደጋ ውስጥ የከተተው፤ ይህ ከእግዚአብሔር መለየትና ተለይቶ መቆም ያመጣው ጣጣ ነው::

<u>እየወረደ መሄድ፤</u>

ከተለየ በኋላ ደግሞ፤ ቃሉ ወጣ ሳይሆን፤ <u>ወረደ</u> ነው የሚለው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በበጎ ጉኑ የሚገለጸው ተለይቶ ወጣ እንጂ፤ ተለይቶ ወረደ የሚለውን አይደለም:: ይህንን በአብርሃም ሕይወት ስናየው፤ ዘፍ.12፡1-2 ላይ ‹‹ ከሀገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ:: ታላቅ ሕዝብም





አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብርዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን፡!›› የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ይሁዳ እዚህ ላይ አላገኘውም::

ወደ ላይ ለመውጣት ብዙ መሰናክሎች ከማስተዋል ጋር ማለፍ ይጠይቃል:: ጉዞና ሂደቱም አድካሚ ነው:: እዚህ ላይ ግን፤ ተለይቶ ወረደ ነው የሚለው:: የወረደው ደግሞ፤ የባለብዙ ተስፋና የቃል ኪዳኑ ባለ ራእዩ ይሁዳ ነው::

ብዙዎች ከነበሩበት ደረጃና ኃላፊነት ሲወርዱ፤ ክብራቸውን፣ ሞገሳቸውን፣ መንፈሳቸውን፣ ጸጋቸውን፣ በረከታቸውን፣ ሀብታቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ተቀባይነታቸውን፣ ተወዳጅነታቸውን፣ ማዕረጋቸውን፣ ሥልጣናቸውን ወዘተ... ሲያጡ ይሚሸሻሉ::

ለዚህ ጉዳይ ደግሞ፤ <u>የመናፍስቱ ጥቃትና</u> የራሳቸው መንፈሳዊ ድክመት <u>የግለሰቦቹ አስተዋጽኦ</u> በዋናነት የሚጠቀስ ነው:: ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ይሁዳ፤ በልዑል አምላክ እግዚአብሔር የተመረጠ በበረከትና በጸጋ ውስጥ የሚያልፍ፤ ያባቶቹን ታሪክ የቃል ኪዳን ኑሮና ቤት የሚያሳምር ነው:: በወደፊቱ ራእይ ውስጥ ደግሞ፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከድንግል ማርያም የሚወለደው ከእርሱ ዘር ውስጥ ነው:: ግን፤ ይሁዳ ወረደ::

በዚህ ጊዜ ለዲያብሎስ ትልቅ የደስታ አጋጣሚ ነው:: ይሁዳ ከወረደ መጀመሪያ የሚረሳው የአባቶቹንና የእናቶቹን የእምነትና የምስጋና መንገድ ነው::

ሕይወቱ በብዙ አቅጣጫ ደክሟል:: ከታሪክ አንፃር የአብርሃምን፣ የይስሐቅን የቅድመ አያቶቹን መንፈስና በረከት በመሸለም ይኖዝ የነበረውን ያዕቆብን የተካው ልጁ ይሁዳ ግን ተለይቶ ወረዷል:: ምንጊዜም አንዱ ትውልድ ሲያልፍ ወይም ሲደክም፤ ተተኪው ትውልድ በክፉ መንፈስ በኩል እጅግ ወደተወሳሰበ መንገድ የአኗኗርና የእምነት ታሪክ ውስጥ የመግባቱ ጉዳይ፤ የተለመደ ነው::

በዚህ ወራት እንዲህ ሆነ። «ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ ወረደ፣ ስሙን ኤራስ ወደሚሉት ዓዶሎማዊውም ሰው ገባ።» ዘፍ. 38÷1 ሲወርድ ያገኘው አገር አዶሎምን ነው። <u>አዶሎም</u> ማለት ከእብራይስጥ ወደ አማርኛ ሲመለስ፤ <u>«የስደተኞች መንደር»</u> ማለት ነው።

ይህ ለባለራእዩ ሰው ለይሁዳ አሳዛኝ ምዕራፍ ነው። ብዙ ጊዜ ይህንን መንገድ የእግዚአብሔር ሰው ይሄድበታል። <u>**ቤተልሔም**</u> ከሚሄድ ይልቅ ወደ <u>**አዶሎም**</u> መሄድን ይመርጣል። ወደ <u>**ቤቴል**</u> ከመውጣት ይልቅ፤ ወደ <u>**አዶሎም**</u> መውረድ ይመርጣል። በእኛም ዘመንና ዕድሜም እንዲሁ ሆኖአል።

መለየትና መውረድ ሲጀመር የሚታየው፤ ኢይዝራኤል፣ ቤተልሔም፣ ኤፍራታ፣ ቤቴል ወዘተ… አይደለም። ዛሬ እያንዳንዳችን የወረድንበትን መንገድ ስናስተውል አዶሎም ይታየናል። በአሁን ዘመን ሰዎች እቤታቸው ቁጭ ብለው በሃሳብ ይሰደዳሉ። ውጭ አገርን ይመኛሉ። የዚህ ትውልድ አንዱ መለያ፤ ሰው ከቤቱ ሳይወጣ፤ በሕሊናና በልቦናው መሰደድ፣ ሆኖአል።

የተስፋና የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞህ ሲጣመምና አባቶች ካቆዩልህ በረከት ስትርቅ፤ የምትገኘው <u>በስደት</u> ላይ ነው። በየጊዜው ለልዑል አምላክህ ተንበርክከህ የመንፈስ ጠላቶችህን መዋጋት ሲያቅትህ፤ የምትገኘው አዶሎም ውስጥ ነው።

ዛሬም እኛ ከአገራችን ሰዎች ይልቅ፤ ስለውጭው ዓለም ጀግኖች፣ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራኖች፣ ጄኔራሎች፣ ከበርቴዎች ወዘተ… ብናውቅና ብንማር ደስ ይለናል። ሥራ ለመግባት በምንፈተንበት ጊዜ የምንጠየቀው ጥያቄዎች ስለውጭው ዓለም ሰዎች ብቻ ነው። የፈታኙና የተፈታኙ ልብ ወደ ውጭ ወደ ስደት ከሆነ ቆይቷል።

በዚህ የተነሳ እኛም ሰዎችን የምንመዘነው፤ በውጭ ሰዎች ዝናና ታሪክ ላይ ነው። እነዚያ ከአምልኮትና ከመንፈሳዊ በረከት ርቀው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።





በክፉ መንፈስ ፈተና እጅ ውስጥ ከመግባት ጋር ተያይዞ፤ እቤት ቁጭ ብሎ፤ አልጋው ላይ ተኝቶ ይሰደዳል። የአካል፤ የአእምሮ ስደት፣ ለእውቀት፣ ለሙያ፣ ለገንዘብና ለእንጀራ ስደት ተጋልጦ፤ የምስጋና ተስፋው ቃል የራቀው ትውልድ ሙሉ ለሙሉ ከበረከቱ ተሚጦ ወጥቶ፤ እንደገና ወደክርስትና ለመመለስ አቅም አንሶት በጠላቱ ሰይጣን ላይ መረጃ አጥቶ፤ በክፉ መናፍስት እጅ ውስጥ ገብቶ፤ ተወልዶአል። አብሮት አድጎ፤ እንዴት የተቃና መንፈሳዊ አስተሳሰብና ሕሊና ኖሮት፤ በቤተልሔም ሊኖር ይችላል?

የተቃና መንፈስ ይዞ፤ የእስራኤል ነቢያት በኖሩበት፤ ኤልያስና ሙሴ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተገለጡበት መንፈሳዊው የደብረ ታቦር ተራራ ላይ እንዴት ሊቆም ይችላል? ማቴ.17÷1-5

መጀመሪያ ከተለየህ የግድ አማራጩ መውረድ ነው። ስትወርድ የሚጠብቅህ ቤት፣ ኑሮ፣ ገንዘብ፣ እውቀት፣ ታሪክ እዚያው ስደተኞች ሰፈር ነው። ብትማር፣ ብትሰራ፣ ብታገኝ፣ ብታጣ፣ ብትበላ፣ ብትጠጣ፣ ስደተኛ ነህ። ዛሬም ከዓመታት በኋላ፤ ልጆቻችን ሁሉ ሀሳባቸው ውጭ አገር ሆኖአል።

በፊት የምንታወቀው **«ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።»** በሚለው የዳዊት ራእይ ውስጥ ነው።

ሰይጣን የቀደመበት ጉዳይ ላይ ትኩረት ስላላደረግን፤ በሕይወታችን ውስጥ የማጥፋቱን ዕቅድና ኑሯችንን የመያዝ ጠባዩንና በሥልት ሲያጠቃን አልነቃንበትም። አንዳንዶቻችን ነጻነት አለን ብለን እንከራለን። ክፉ መናፍስት እኔን አይደፍረኝም ብለን እናስባለን።

ቤተክርስቲያ እሄዳለሁ፤ ወንጌል እሳለማለሁ፤ አስቀድሳለሁ፤ እጸልያለሁ፤ እጾማለሁ፤ እስግዳለሁ እንላለን። ግን ያለነው አዶሎም ውስጥ ነው። <u>የስደተኞች መንደር!</u>

ክፋት፣ ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ቅናት፣ ሐሜት፣ ዘራችን ነው። ካልተቃወምን ካላማንና ሌሎችን ካላቆሰልን፤ ጨዋታና ወሬያችን

ሐ. <u>ቀለበት፡-</u> የቃል ኪዳን ተስፋ፤ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም፤ የሚመጣው የብርሃን ኃይል፤ የሰማይ ቸርነት መገኛ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ኃይልና ጉዞ፤ በአካል መታየትና የቃል ኪዳን ምልክት ነው። ይሁዳ እነኚህ ሶስቱን በረከቶቹን ይዞ ነው፤ ወደ አዶሎም፤ ኤራስ ቤት የወረደው!

## <u>የሰው ልጅ የቁልቁሊት ኑሮ</u>

ወደ ኤራስ የሚወስደው መንገድ ቁልቁለት ነው። ከዚያም በኋላ ይሁዳ ጋብቻውን ሲመሰርት፤ የሴዋን ሴት ልጅ አየ። <u>‹‹ሴዋ››</u> ማለት ትርጉሙ **<u>ቁልቁል</u>** ማለት ነው።

በዘፍ. 38 1÷15 ላይ ያለው ቃል እንዲህ ይላል። ‹‹ **በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ ወረደ፣ ስሙን ኤራስ ወደሚሉት ወደ ዓዶሎማዊው ሰው ገባ። ከዚያም ይሁዳ የከነዓናዊውን የሴዋን ሴት ልጅ አየ፤ ወሰዳትም፣ ወደ እርስዋም ገባ። ፀነሰችም ወንድ ልጅንም ወለደች፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራችው። ደግሞም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች፤ ስሙንም አውናን ብላ ጠራችው። እንደገና ደግሞ ወንድ ልጅን ወለደች፣ ስሙንም ሴሎም ብላ ጠራችው፤ እርሱንም በወለደች ጊዜ ክዚብ በሚባል አገር ነበረች።** ››

ከዚህ በኋላ ይሁዳ፤ ራእዩ እዚያው አካባቢ ላይ የተወሰነ ሆነ። የሚያየው ቁልቁል እንጂ በሥፋት የማየትና በአድማስ ላይ የመቆም ዕድል የለውም። ቢመለከትም፣ ቢያስብም፣ ቢያቅድም ቁልቁል ነው። መውረድ ከጀመርክ፤ የሚጠብቁህና የምታገኛቸው ሁሉ ወደ ታች የሚያወርዱህ ናቸው። አንዴ ጫት መቃም ከጀመርክ እየመረቀንክ፤ ሕሊናህ እየደነዘዘ፤ ውስጥህ እየተበላሸ ሱስ፣ ጠንቋይ፣ ዛርና ውቃቢ ውስጥ ሰተት ብለህ እንደ ቀልድ ትገባና፤ በቀላሉ ለመውጣት ትቸገራለህ። በዚያው ቁልቁል ትወርዳለህ።



በማስዳ መያ'ዝ

ቁማር፣ መጠጥና ሴሰኝነትም ከጀመርክ፤ የሱስ አመል እንደ ዋዛ እያሳሳቀ በዚያው ቁልቁል ይዞህ ትወርዳለህ።

እናም ሴዋ ሲወለድ እናትየው ገበያ ውላ ወደ ቤቷ ስትመለስ ቁልቁለት መንገድ ላይ ምጥ ያዛትና እዚያው ወለደችው። ከዚያ በኋላ የልጇን ስም ‹‹ **<u>የቁልቁሊት ልጅ፤ ሴዋ</u>** ››አለችው።

አመስጋኙ ሰው ቁልቁል ወርዶ ሚስት ሲፈልግ፤ ያገባት ልጅ ደግሞ፤ የቁልቁሊቱን ሰው ልጅ ነው። አያችሁ! አንድ ጊዜ ከወረድን በቀላሉ እንደማንመለስ? ከታሪካዊ እውነት፣ ከመንፈሳዊ ተስፋ፣ ከአባቶች የቃል ኪዳን ፍቅር፣ ከወገናዊነትና ከአገር ፍቅር ከተለየንና አንዴ አምላክን ከተውን፤ በቀላሉ ወደ እርሱ እንደማንመጣ! ሕይወታችን እንዴት እንደሚቀየር! በክፉ መንፈስ እንዴት እንደምንያዝ፤ የይሁዳ ታሪክ ማረጋገጫ ነው። የወረደው ሰው ይሁዳ፤ ‹‹ .... **የሴዋን ሴት ልጅ አየ፤ ወሰዳትም፣ ወደ እርሰዋም ገባ። ፀነሰችም ወንድ ልጅንም ወለደች፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራቿው።**›› ይለናል፤ ቃሉ። **<u>ዔር</u>** ማለት፤ **<u>የክፋት ልጅ</u>** ማለት ነው።

አሁንም ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም <u>አውናን</u>፤ ብላ ጠራችው። <u>አውናን</u> ማለት ደግሞ፤ <u>መንቻካና ግትር</u> ማለት ነው።

እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ ጸነሰች፤ ወለደችም፤ ሥሙንም ‹‹<u>ሴሎም</u>›› ብላ አወጣችለት። ሴሎም ወይም ሼሎም (በእብራይስጥ) ማለት ደግሞ ‹‹<u>ቷዳጊ</u>›› ማለት ነው። ሴሎም የተወለደው ይሁዳ ከነቤተሰቡ አዶሎምን ለቆ <u>ክዚብ</u> ወደ ተባለ አገር ከገባ በኋላ ነበር። አሁን ይሁዳ አገር ቀይሮ ክዚብ ገብቷል። **<u>ክዚብ</u>** የሚለው ቃል በእብራይስጥና በአረብኛ ተመሳሳይ ትርጓሜ አለው። <u>የውሸት አገር</u> ማለት ነው። ሴሎም የውሸት አገር ተወለደ። ከውሸት እግዚአብሔር ይማረን፤ እስተዋይነቱም ይሰጠን።

## 4.4 <u>የክፋት ልጅ (ዔር)</u>

ዔር ማለት የክፋት ልጅ ነው ብለናል። የክፋት ልጅ ቁልቁል ሲሄድ፤ ከሰማይ አምላክ ሲለይ፤ ከበረከት አምባ ሲወጣ፤ የሃይማኖትና የእምነት ፍቅር ከሰውነቱ ተለይቶ፤ የኑሮና የሥጋ ፍቅር፤ የወንበርና የሥልጣን፤ የጥቅምና የንዋይ ፍቅር ሲይዘው፤ የሚወለደው የክፋት ልጅ ይሆናል ማለት ነው።

ጸሎት ሲቋረጥ፤ የሃይማኖት ተስፋ ከባሕርያችን ሲርቅ፤ ማተባችንን ስንበጥስ፤ የሚወለደው የክፋት ልጅ ነው። ይሁዳ ሕይወቱን ለአደጋ የጋበዘው፤ ክፉ መንፈስ ነው። <u>የዓይን-ጥላ ልክፍት</u> አድሮበት ወደታች አወረደው። ዛሬ በክፋው ጠላት ተይዘው የምናገኛቸውና የምናያቸው በርካታ እህቶችና ወንድሞች፤ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲሰቃዩ የነበሩ ናቸው።

ዛሬ ብዙዎቻችን የክፉ መናፍስት ሰለባዎች ነን። የመተቱ፤ የሚርቱ፤ የሰላቢው፤ የዛሩ፤ የውቃቢው፤ የጨሌው መንፈስ ወዘተ... ሁሉ ሕይወታችንንና ቤታችንን ጎድቶታል። ለምን? ከመሠረቱ ከሃይኖማት ተስፋ ወጣን፤ ጸሎት ረሳን። እቤታችን፤ የመንበርከኪያና የመጸለያ ቦታ የለንም። ለልጆቻችን የምናሳየውና የምናስተላልፈው የአምልኮት ጠባይና ሕግ የለንም። ምግብ በልተን መተኛት ሆነ። በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር አምላክ ሥፍራ የለንም።

በቅዱስ ጴጥሮስ መልዕክት ላይ፤‹‹**ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራል**›› የሚል መልዕክት እናገኛለን።

ዛሬ በክፋው መንፈስ ያልተዋጠ ማን አለ? ቁልቁል በመውረድ ሕይወት ውስጥ የክፋት ልጆች ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል።

ጎረቤት ለጎረቤቱ ክፋት ይመኛል። በእርሻ ማሣ በድንበር ላይ ፣ በንግዱ ሥፍራ፣ በትምህርት ቤት፣ በቢሮ፣ በሰላም ወጥቶ መግባት ላይ ወዘተ ... ክፋት እንመኛለን።





ታዲያ እኛስ **ዔር** ወይም **የክፋት ልጅ** ከመሆን ምን ይለየናል? መውረድ ለጊዜው የሚመች ቢመስልም፤ የማይታዩና የተወሳሰቡ ፈተናዎች ከፊት አድፍጠው የሚጠብቁበት ሥፍራ ነው።

እያረፍክም ቢሆን ትወርዳለህ። የታሪክ ክንውንህ ግን፤ ከሞቱት የመቃብር ሰዎች አይለይም።

ይህ በቢያ **በዔር** ዘመን ላይ ብቻ የቆመ ታሪክ ሳይሆን፤ በእኛም ዘመን ውስጥ ቀጥሎ፤ በተመሣሣይ የሕይወት ጎዳና ላይ እንገኛለን።

## 4.5 <u>መንቻካና ግትር ልጅ (አውናን)፤</u>

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው፤ ቀጥሎ የተወለደው ደግሞ አውናን ነው። እርሱም፤ መንቻካና ግትር የተባለው ነው። የባሰ እንጂ የተሻለ አልተገኘም።

ወደ ራሳችን ስንመለስ፤ ጠባያችን እንዴት ነው? እንኳን ለሰው፤ ለእንስሳውና ለተፈጥሮም አይመችም። አመላችን ተበሳሽቷል። በመንፈሳዊና በሥነ-ምግባራዊ ሞራል ተከትክቶ የማደግ የቆየው የእምነት መንገድና ሕግ፤ ተቋርጧል።

ታላላቅ የሆኑ የመንፈሳዊ ጸጋ ስጦታዎች ከሕይወታችን ርቀዋል። አሁን የሚጠብቀን የመንፈስ አደጋ ይሆናል ማለት ነው።

ብዙዎቻችን መንቻካና ግትሮች ነን። ለእርቅና ለምክር አንመችም። ለሽምግልናና ለማስታረቅ አንመረጥም። ለሰላምና ለመተሳሰብ አንቀርብም። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ነው፤ ወደፊት መልካም ነገር የምንጠብቀው? አይደለም። ይህ ጠባይ መለወጥ አለበት። ሊለወጥ የሚችለው ደግሞ፤ በአምላካችን፤ በሰማይ አባታችንና በቅዱሳን መንፈስ፤ በሰማያዊው ሠራዊት ስንደገፍ ብቻ ነው።

እውቀታችን፣ ትምህርታችን፣ ጠባያችን፣ ሥራችን ሁሉ፤ የውሸት ታዳጊ ሆኖብን፤ እኛም ክዚብ ሆንን ማለት ነው። በጎሣና በዘር ተከፋፍለን በመናቆር፤ ለዲያቢሎስ ጥቃት በር ከፍተናል።

እናሳድጋለን ብለው ወልደው ማሳደግ ያቃታቸው ስንት የምናውቃቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ገና ሲወለዱ፤ እንዲህ ሆኗል። ጊዜው፣ ዘመኑ እንዲህ ይላል። **የውሸት ታዳጊ!**

**ሰቱም** የይሁዳ ልጆች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐረግ ትውልድ **አይመጡም**። መንገድ ላይ ይቀራሉ። እኛም፤ ከክርስቶስ ሥጋና ደም ተለይተን እንዳንቀር፤ **እግዚአብሔር ሆይ! ከመንፈሳዊ** ዘርህ፣ **እባክህ፣ መንገድ ላይ የሚቀር ትውልድ አታድርገን** እንበለው።

የይሁዳ ልጆች፤ ወደ ድንግል ማርያም ሐረግ ትውልድ **አይመጡም**። በረሃ ላይ ይቀራሉ፤ ቁልሰቁል ተወለደውና አድገው፤ **ቁልቁል** ይቀበራሉ።

አንዱ **<u>የከፋት</u>** ልጅ ነው። ሁለተኛው <u>መንቻካና ግትር</u> ነው። ሶስተኛው **<u>የውሸት ታዳጊ</u>** ነው። እነዚህ ሶስቱ ልጆች በዚያ ዘመን ውስጥ ከኖሩ ነገዶች ውስጥ ናቸው። የተወለዱት ደግሞ፤ **የእግዚአብሔር** በረከት ከተቀበለው ከታላቁ ሰው **ከይሁዳ** ነው። ይሁዳ ስሙና ኑሮው አንድ አልሆነም። ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፤ **ይሁዳ ማለት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ!** ማለት ነው።

**ከዘርና** ጎሰኝነት አንጻር ሲታይ፤ ከአንዱ የአገራችን ጫፍ **የመጣች** አህያ፤ ከሌላው የአገራችን ጠርዝ ከመጣች አቻዋ ጋር፤ ተስማምተው ይግጣሉ። ከምዕራብ የመጣ በሬ፤ ከባሌም ይሁን ከጎንደር ከመጣ በሬ ጋር፤ አንድ ላይ ብታሰማሯቸው፤ ተስማምተው ይበላሉ።

**ከዚህ** ስንነሳ፤ ትክክለኛ ድምዳሜ ነው ባይባልም፤ ምሳሌው **እንስሶች** ከእኛ በተሻለ ሁኔታ ያላቸውን ኅብረትና አንድነት ያሳያል።





እኛ በክፉ መንፈስ ተጠምደን፤ መተሳሰቡ ቀርቶብን ልዩነትንና አለመቻቻልን በማራገብ የክፋት ልጅነትን እናገለግላለን። ከሥራችንና ከጠባያችንም አንጻር ሲታይ፤ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚጠብቅ የሚመስል ሕይወት ይዘናል። የሰማይ አምላክ ይማረን።

ተዛብተን ነው ያደግነው፤ ባልሆነ አቅጣጫ ላይ ቆመናል። ት/ቤቶቻችን የክፉውን መንፈስ ምልክት ለጠባያችን ሰጥተውታል። ሳይንስና ፍልስፍና፤ የጥርጣሬ ማዕበልን በውስጣችን ለቀው፤ ሃይማኖታዊ ጸጋን ከሕይወታችን ውስጥ አሟጠን እንድንጥል ገፋፍተውናል።

ዛሬ በሁሉም መስክ መልስ አለኝ የሚለው ሳይንስ፤ መላው የዓለም ሕብረተሰብ ከእግዚአብሔር እንዳይጠይቅና መልስ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ፤ የሰው ልጅ ሁሉ በሰውና በሰይጣን እጅ ውስጥ እንዲወድቅ፤ በአንድ በኩል አስተዋጽዖውን አበርክቷል።

የመናፍስቱ ውጊያ ለሳይንሱ ዓለም ተረት ተረት፤ ወይም ድራማ ነው። እውነታው ግን፤ ከዚህ የራቀና ይህን አመለካከት የሚጋራ አይደለም። እየኖርን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ለምን? ዲያብሎስ በታላቅ ቁጣ ወርዷል። በምድርም ላይ ሙሉ በሙሉ ነግሷል። ሉቃ. 18÷8 ‹‹**ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?** ›› ይህ ምዕራፍ ለሰው ዘር፣ ለቤተ-እግዚአብሔርና ለዓለም የተተወና ያልተመለሰ ጥያቄ ነው።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን እንዴት ነው ሰይጣንን የምንጥለው? የዲያብሎስ ሠራዊት የሚዋረደው፤ በዚህ አቋም፣ ሁኔታና የተልፈሰፈሰ ጊዜ ነው? አይደለም! ቃሉ ቢመረንም፤ እውነታው ግን፤ እነዚህ ሶስቱ የይሁዳ ልጆች ጠባይ፤ አሁን ያለውን ትውልድ ገጽታ፤ በቀጥታ የሚያመለክቱ ናቸው።

ይቀናዋል፡፡ ልጆቹ የሞቱበት ምክንያት ቀጣው ከእግዚአብሔር እንደመጣ ገና ስላልገባው ችግር መስላ የታየችው ትዕማር ነበረች፡፡

ምክንያቱም፤ ይሁዳ ቁልቁል ስለወረደ፤ አስተሳሰቡም እንደዚያው እየወረደ ነው የመጣው፡፡ የተሰጠውን በረከት ወደታች አውርዶ ኑሮውን ስለለወጠ፤ ሕይወት በእርሱ ዘንድ የተሳካ አልነበረችም፡፡

ትዕማር ከቀደሙት ባሎቿ ከዔርና ከአውናን ጋር በኖረችበት ዘመን ሁለቱም በየተራ ሲሞቱ አልቅሳለች፤ አንዳንዴ በእንደዚህ ዓይነት አሳዛኝ ጎዳና ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልፋል፡፡ ይህ ሁሉ ለምን? ሆነ ስንል፤ ችግሩ ወደ ይሁዳ ይመራናል፡፡

- ይሁዳ ራእዩን ተወው፤
- የምሥጋና ጊዜውን አቋረጠ ፤
- የአባቶቹን መንገድና የተሰጠውን ተስፋ እየረሳ የአምልኮት ክበር ተለየው፡፡

ስለዚህ አስቸጋሪ ልጆችን አፈራ፡፡ በዚህም የለቅሶ ጊዜ፤ በረከትና ተስፋ አጥቶ፤ የሚጨነቅበትን ኑሮ ጀመረ፡፡ ሁለንተናዊ የሆኑ ግቦቹ ሁሉ ጠፉበት፡፡

ምናልባት እኛ ወደ ኋላ ልናስብ የምንችልበት የአባቶቻችንን መንፈሳዊ አቅጣጫና የተስፋውን ኃይልና የቃል ኪዳኑን መንገድ ለማስተዋል ጊዜ ካገኘን፤ ዕድላችን በበረከት በኩል ሰፊ ይሆናል፡፡

ከብዙ የአሳርና የመከራ ኑሮ በኋላ ትዕማር ወደ አባቷ ቤት ተመለሰች፡፡ የትዕማር ኑሮ ‹‹ሀ›› ብሎ የሚጀምረው፤ በፊት ከሄደችበትና ከገባችበት ከከዚብ አገር ሕይወትዋ ሳይሆን፤ አሁን ከተመለሰችበት የአባቷ ቤት ውስጥ፤ እንደ አዲስ ይሆናል፡፡

በትዕማር ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ትልቁ ጉዳይ፤ መረጋጋት ነው፡፡ይህንን መንገድ የምትይዘው ደግሞ፤ የውሸት አገር (ከዚብ) እና የስደተኞች መንደር (አዶሎም) ውስጥ ሆና አይደለም፡፡





እግዚአብሔር በትዕማር አባት ቤት ውስጥ ሆኖ ለእርስዋ ልዩና ታሪካዊ ሥራውን ይሠራል፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ <u>የይሁዳ ሚስት የሴዋ ልጅ ሞተች</u>፡፡ ይሁዳ መጀመሪያ ልጆቹን፤ ቀጥሎ ደግሞ ሚስቱን በሞት ተነጠቀ፡፡ ብቸኝነቱ ለይሁዳ ከባድና አስቸጋሪ ሆነ፡፡ የይሁዳ የቁልቁሊት ኑሮና ጉዞ፤ የበለጠ እያወረደው ነው፡፡

**‹‹ይሁዳም ተጽናና፤ የበጎቹን ጠጉር ወደሚሸልቱት ሰዎችም ወደ ተምና ወጣ፤ እርሱም ዓዶሎማዊው ወዳጁም ኤራስ፡፡ ለትዕማርም፡- እነሆ አማትሽ ይሁዳ የበጎቹን ጠጉር ይሸልት ዘንድ ወደ ተምና ይወጣል ብለው ነገሩአት፡፡›› ዘፍ 38፥12-13**

የሚስቱ መሞት የአዶሎምና የከዚብ አገር ማብቂያ እና የልዑል እግዚአብሔር ይሁዳን ለክብሩ የመፈለጉ መንገድ የተገለጠበት ወቅት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የፍለጋና የጥሪ መንገድ ውስጥ <u>ሶስቱን</u> እንመልከት፤

ሀ. እግዚአብሔርን እያለመከ በጥንቃቄና በመንፈሳዊ ጽናት ለኖሩት ተጨማሪ የቅድስና በረከቶችን በመስጠት፤ የጠላትን ኃይል በመስበር የታሪካቸውን አቅጣጫ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ትውልዱን ለዘለዓለም መባረክ ነው፡፡

ለ. ከእግዚአብሔር ከተለዩ በኋላ በተለያየ ፈተና ውስጥ ወድቀውና በክፉ መንፈስ ተይዘው ሲመሩ፤ ክብሩን ሲንቁና ኃይሉን ሲረሱ የሚገኙትን ትውልዶች ሁሉ፤ በሕይወታቸው ውስጥ ቀዳሚ አድርገው እንደ አምላክ የሚያመልኩትን ጥቅምና የሚያዩትን ሁኔታ መቀየር ነው፡፡ ሰዎች እግዚአብሔርን አስበው ወደ ክብሩ እንዲመለሱ፤ ከተስፋውም ቃል ኪዳን እንዲገናኙ ማድረግ፤ አንዱ የእግዚአብሔር መንገድ ነው፡፡ ይሁዳ የሚስቱ መሞት፤ አለኝ የሚለውን የማጣት ምልክት ነው፡፡ ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን

‹‹ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፤ የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ:: ›› ምሳ. 18÷21

በሰለስቱ ደቂቅ ዘመን፤ ናቡከደነፆር ያዘጋጀው እሳት ነበር:: እኛም አባቶቻችን ከነገሩን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከሥጋውና ደሙ ከማሕተሙ ፍቅር ስንወጣና ከልዑል እግዚአብሔር ስንለይ ሌላው የምናዘጋጀው፤ የሚቃጠልበትን እሳት ነው::

አሁን ትዕማር በእሳት እንድትቃጠል ተወስኗል:: ሰው ሁሉ በተሰበሰበበት ሥፍራ ላይ፤ **ከመቃጠሌ በፊት ይህንን ውሣኔ በእኔ ላይ ያስተላለፈው ሰው ይሁዳ፤ ይምጣ** አለች::

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው፤ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ተስፋ ከያዙ ሰዎች መካከል፤ ከይሁዳ የሚበልጥ የለም:: ይሁን እንጂ፤ ወደ አዶሉም ከወረደ በኋላ፤ የምስጋናውን ጊዜ አቋርጦ፤ የአባቶቹን ራእይ ንቆና ዘንግቶ፤ **ከማለዳው ሲወርድ** ያገኘው ትውልድና የኖረበት ታሪክ፤ በአመዛኙ መራራ ሆኖብታል::

ይሁዳ ትዕማር ትቃጠል፤ ሴሎምን አልሰጣትም ብሎ፤ የትውልድ ስስት ጀመረ:: ብዙ ሰዎች ዛሬ በስስት ያሣደጓቸው ልጆች፤ ቤተሰባቸውን ሲያምሱ ይታያሉ:: አንተ ብላ ልጄ እኔ ይቅርብኝ ብላ ልጇን ያጎረሰች፤ እንዳይበርድሽ አንቺ ልበሺ ልጄ ብላ ልጇን ያለበሰች እናት፤ ዛሬ ተራቁታለች፤ ተንቃለች::

ወላጆች፤ የእግዚአብሔርን ስም አልጠራንም፤ ፍቅሩንና ክብሩን አላሳየንም:: ስለዚህ አውጥተን አውርደን፤ የምናገኘው ሌላው የሚቃጠልበትን መንገድ ነው::

ይህ ሁሉ መተትና ሟርት ከየት መጣ? ተቃጠሉ፣ ይቃጠሉ ተብሎ ልከው ያስገቡብን አይደለም እንዴ? ዓይነ-ጥላው ለምን ሕይወታችን ውስጥ ሥር ሰዶ ተቀመጠ? ዛርና ውቃቢ ለምን ነፍሳችንን ወጥሮ ያዘው? ዕድላችን እስኪጨልም ድረስ ለምን ይፋለመናል? የመቃጠሉ አካል አይደለም? ወደ ገሃነመ-እሳት





የሚሔደው ዲያብሎስ ዛሬ በሕይወታችን ላይ፤ እዚያ ክፉዎችን የሚጠብቀውን እሳት፤ እዚህ እኛ ላይ ለኩሶታል:: የዚያን መንፈስ ክብሪት እየጫርን፤ ጎረቤቶቻችንን፣ ዘመዶቻችንን፣ ይበልጡናል ያልናቸውን ሁሉ በቅናት ተነሳስተን እናቃጥላለን::

ይህ ከሃይማኖት ተስፋና በረከት፤ ርቆ የወረደ ትውልድ ሊያመጣ የሚችለው አደጋ ነው::

ትዕማር ትቃጠል ብሎ የፈረደው ዳኛ ይሁዳ፤ የራሱን ውሳኔ ለማስፈጸም፤ በሚንቀለቀለው እሳት ፊት ተገኝቷል::

ከዚህ በኋላ ትዕማር እንዲህ አለች፤ ‹‹ **እርስዋም ባወጡአት ጊዜ ወደ አማትዋ እንዲህ ብላ ላከች፡- ለዚህ ለባለ ገንዘብ ነው የፀነስሁት፤ ተመልከት ይህ ቀለበት፣ ይህ አምባር፣ ይህ በትር የማን ነው? ይሁዳም አወቀ፡- ከእኔ ይልቅ እርስዋ እውነተኛ ሆነች፤ ልጄን ሴሎምን አልሰጠኋትምና አለ:: ደግሞም አላወቃትም:: በመውለጃዋም ጊዜ እነሆ መንታ ልጆች በሆድዋ ነበሩ:: ስትወልድም አንዱ እጁን አወጣ፤ አዋላጂቱም ቀይ ፈትል ወስዳ በእጁ አሰረች፡- ይህ መጀመሪያ ይወጣል አለች:: እንዲህም ሆነ እጁን በመለሰ ጊዜ እነሆ ወንድሙ ወጣ፤ እርስዋም፡- ለምን ጥሰህ ወጣህ? አለች፤ ስሙንም ፋሬስ ብላ ጠራችው:: ከእርሱም በኋላ ቀይ ፈትል በእጁ ያለበት ወንድሙ ወጣ፤ ስሙም ዛራ ተባለ::** ›› ዘፍ 38÷25-30

ይሁዳ ከአምሳ አንድ ዓመት በኋላ ንስሐ ገብቶ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነት ተናገረ:: ‹‹ **ከእኔ ይልቅ እርሷ እውነተኛ ሆነች::** ›› እውነቱን ለማመን የተገደደው፤ በእውነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ባዶነቱን ስለተረዳውና የትዕማር ተስፋ በእውነት ሕይወት ስለተገለጠ እንዲሁም የቃልኪዳን መሣሪያዎቹ በእጇ ስላሉ ነው::

በይሁዳ ታሪክ ውስጥ የእውነት መንገድ ለብዙ ዘመናት ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ፤ የተወለዱት ልጆች የገጠማቸው ችግር እና ፈተና፤ ምን ያህል ከባድ እንደነበረ፤ ለማስታወስ አያዳግትም::

ስለዚህ ይሄን ሁሉ ለማለፍ፤ በሕይወታችን፣ በአባቶቻችንና በመሪዎቻችን፤ በአጠቃላይ በሕብረተሰባችን ውስጥ ፋሬስ መወለድ አለበት።

ፋሬስን ለመውለድ፤ ይሁዳና ትዕማር የተጓዙትን ጉዞ ከልባችን በማስተዋል የምንረዳው ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ የምንኖረው ሕይወት እንዲሆንና የመንፈሳዊ የሕይወት ጉዞ አቅጣጫ ከእውነት አንጻር የቱን ያህል ርቀን ቢጋብቻ፤ በተተኪ ትውልድ በአርአያነት ምሳሌ እጅግ እንደተጎዳን የምናገናዝበው፤ አሁን ያለውን ትውልድና ዕጣ፤ ጊዜያዊ አስተሳሰብና የፍላጎት መሻቱን ረጋ ብለን ስናስተውል ብቻ ነው።

ዛሬ በእኛ ዘመን ብዙ ያልተጣሱ፤ ወይም ጥሰን ያላለፍናቸው ከፊታችን የራቁ፤ ለመጣስ ብዙ መንከራተትን የሚጠብቁና ዕድሜያችንን ሙሉ የሚፈታተኑ ችግሮች እንዳሉብን፤ ማንም ሰው የሚያምነው ጉዳይ ነው። የተደበቀብን ነገር ቢኖር እነዚህን ችግሮች ጥሰን ለማለፍ የምናካሂዳቸው ፍጥጫዎች፤ የምንፈክራቸው መፈክሮች እየበዙ በሄዱ ቁጥር፤ ችግሮቹም የዛኑ ያህል እየበዙ መምጣታቸው፤ የዓለም መሪዎችም ሳይቀር ስጋታቸው ሆኖአል።

ዛሬ እኛ ብዙ ዓመታትን አሳለፍን የምንሰማቸውና የምናያቸው የችግር ጩኸቶች፤ ባለማቋረጥ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ፣ መሃይምነት፣ በሽታ፣ ድህነት፣ ረሃብ፣ እርዛት፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ጦርነት፣ እነዚህ ሁሉ መቅሰፍቶች በሁሉም መሪዎች ዘመን የተጮኸባቸው የተረገሙ፤ አልፎም ተርፎ የተነገደባቸውና በሙስና የትርፍ ማካበቻ በመሆን፤ ተጨማሪ ችግሮች ሆኑብን እንጂ፤ ጥሶ የማለፍ መፍትሄ አላመጡልንም።

ስለዚህ ብንወድም ብንጠላም፤ ወይም ፋሬስ መሆን አለብን፤ አልያም ፋሬስ መወለድ አለበት። ፋሬስ የሚገኘው ደግሞ በሃይማኖት የታሪክ ጉዞ ውስጥና በክርስቶስ ሥጋና ደም በኩል ብቻ እንደሚሆን፤ በጸሎትና በንጹህ አምልኮት ማመን ይገባናል።





በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ የሚቀድመው፤ መራራ ነገር ነው፤ ዲያብሎስን ለማሸነፍና የከፋቱን ትርጉም ለማወቅ፤ ብዙ ጊዜ ይፈጅብናል።

ትዕማርም፤ ብዙ መከራ ካሳለፈች በኋላ፤ እግዚአብሔር ተስፋዋን ሞላላት። ይህንን ትውልድ፤ **በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 1÷3** ላይ እናገኘዋለን። **‹‹ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ።››** ይላል። በዚህም ይሁዳ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ትውልድ ውስጥ ገባ። <u>ፋሬስ</u> ማለት <u>ጥሶ የወጣ፤ ጣሰው</u> ማለት ነው።

ችግርን፣ መከራና ሥቃይን ሁሉ የጣሰው ትውልድ፤ ተወለደ። እኛም፤ በእግዚአብሔር በየትኛውም ዘመን የክፋት፣ የክህደት፣ የተንኮልና የምቀኝነት፣ የመተተኝነትና የሟርተኝነት ዘመን ላይ የማይቆም ዘር፣ በእምነትና በረድኤት በኩል፤ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አምባ የሚያመጣና የሚጠጋ ትውልድ ስጠን ብለን እንለምነው። **‹‹ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው። ›› ዮሐ. 1÷12**

ዛሬ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ፋሬስ (ጣሰው) ያስፈልገናል። የአዲስ ኪዳን ጣሰው ከድንግል ማርያም ተወለደ። ከዚያም **‹‹ ዓለም ሳይፈጠር፣ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። ›› ኤፌ. 1÷4**

ዛሬ ጣሰው ለመሆን፤ **‹‹ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ። ›› ሮሜ. 13÷14**

**‹‹ እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ ፀንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።›› ዕብ. 4÷14**

ጉዞዎቹ ላይ፤ በትልቅነታቸው ውስጥ አዙሪት የተጠናወታቸውና ያለባቸው ሰዎች ከፍተኛውን የማስተዳደር ሥፍራ እየያዙ መጡ።

በመሆኑም፤ አክአብ ከሞተ በኋላ ሞአብ በእስራኤል ላይ ዐመፀ። አካዚያስም፤ በሰማሪያ ይዞታውን በመነጽር እየተቆጣጠረና አንድ የሆነ ሥፍራ ላይ አተኩሮ እየተመለከተ በነበረበት ወቅት፤ ከቆመበት የመመልከቻ ሠገነት አናት ላይ ወድቆ ክፉኛ ተጎዳ ። ከሠገነቱ የገፋው፤ ይህ፤ ከባሕሪይው ጋር የተሣሰረው የአዙሪት መንፈስ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም።

ከዚያ በጠና ታመመና፤ አገልጋዮቹን፤ **ሂዱ! ከዚህ ደዌ እድን እንደሆነ፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ጠይቁልኝ!** አለ። የአዙሪት መንፈስ ማለት ይሄ ነው። እንግዲህ አካዚያስ በጣም ትልቅ ሰው፤ ነው። በእስራኤል ውስጥ አለ የሚባል ብርቱ ንጉሥ ነው። ክብሩ የላቀ ነው።

ይሁን እንጂ፤ይህ በታሪክ ውስጥ ትላልቅ አባቶች የመሯትን አገር፤ ታላቁን የእስራኤል ዙፋን የያዘው ንጉሥ፤ ቅዱሳን ነቢያት በነበሩባትና ታሪካዊ አባቶች ባሉባት አገር ውስጥ፤ የተከበረውን ቦታ የያዘው ትልቅ ሰው፤ አሁን የሚጠይቀውና የሚልከውን መልዕክት ስንመለከት፤ ዛሬ በክፉ መናፍስት ትንኮሳ ውስጥ የሚገኘውን፤ የዚህን ትውልድ ደካማ የመንፈሣዊ ሕይወት ጉዞና ልምዶች፤ በገሃድ የሚያሳይና የሚያንጸባርቅ ነው።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ፤ ትልቅነቱ ለእርሱ ለራሱ እንጂ፤ ትንሽ መሆኑን ለማገናዘብ፤ ያ ትንሽ ሰው መረጃ አላገኘም። በትልቅነቱ ውስጥ የጠበቀውን መንፈሳዊ በረከት ንጉሡ ብቻ ሳይሆን፤ ትውልዱም በአዙሪቱ ዛብያ ውስጥ ስላለ፤ ለማየት አልቻለም። ለሚመለከተውና ለሚያስተውለውም ሁሉ፤ በጎ የሆነ ገጽታ በሕይወቱ አልተገለጠም።





## 5.1 የአዙሪት አምላክ ብዔልዜቡል፤

የሆነው ሆኖ የእስራኤሉ ንጉሥ፤ ወደ አቃሮን አምላክ፤ ወደ ብዔልዜቡል መልዕክተኛ ላከ። አቃሮን ማለት ከእብራይስጥ ወደ አማርኛ ሲፈታ፤ አዙሪት ማለት ሲሆን፤ ብዔልዜቡል ማለት ደግሞ፤ የዝንብ አለቃ ማለት ነው።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ፤ በትልቅነት ውስጥ ያለ አዙሪት ትንሽነትን ሲፈጥርና፤ ከጥንካሬና ከትልቅነት ውስጥ፤ ታላቅ ድክመት ሲመነጭ የምናየው። ትልቁን የእስራኤልን ንጉሥ የተጠናወተው አዙሪት፤ የዝንብ አለቃውን እንዲማጸን አደረገው።

ይሄ ሂደት ዛሬ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ፤ አንዳንዴ በትክክል አውቀን፤ ወይም ሳናውቅ፤ ልቦናችን ሙሉ ለሙሉ፤ ወይም በከፊል፤ በመናፍስቱ ተሰውሮብን፤ በእንደዚህ ዓይነት የአዙሪት መንፈስ ገና በማለዳ ተይዘን እንማስናለን።

በሌላ መልኩ የአካዚያስ ወደ እዚህ ዓይነቱ አዝማሚያ መሄድ፤ አሕዛብን ለማስደሰት እንደሆነ ያሣየናል።

አሕዛብ የአቃሮንን አምላክ ማለትም፤ የአዙሪቱን ጣዖት ያመልካሉ። ምክንያቱም፤ ብዙዎቹ በዚህ የአዙሪት ጥላ ውስጥ ስላሉና ስለሚጨነቁ፤ ግብር ይገብሩለታል። የወደፊቱን ሁኔታ በትንቢት መልክ ይገልጽላቸው ስለነበረ፤ ይከተሉታል። ልክ ዛሬ በእኛ ዘመን እንዳለው የዓውደ ነገሥቱ እይታ ማለት ነው።

እዚያ ሀገር ውስጥ ያለውን የአሕዛብን መንፈስ ለማስደሰት ሲባል ብቻ፤ ይሄ ትልቁ ሰው እንዲህ በሆነ የወረደ የአዙሪት ጎዳና ውስጥ ገባ። እኛም ነገ ንስሐ እንገባለን እያልን፤ መንገዱ ከጠፋብን፤ ከተበላሸብን፤ ከደቀቅንበትና ከከሰርንበት የኢኮኖሚ አቋማችን በላቀ ሁኔታ፤ የእግዚአብሔር ከሆነው መንፈሣዊ ሕይወታችን እጅግ ርቀንና ወርደን መገኘታችን፤ የከፋብን አስጨናቂ ጉዳይ ሆኗል።

በሙሉ ሲመዘኑ፤ እያንዳንዱ የነበረውን የሕይወት አቅም ከኑሥነ-ምግባሩ መቶ በመቶ እንደተሰበረ እንረዳለን፡፡

በተፈጥሮ፣ በረሃብ፣ በበሽታ፣ በመሃይምነትና በጦርነት ላይ ብዙ ጊዜ ፎክረናል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ ነጥረው በመመለስ፣ በአጥቂነት ፎክረውብናል፡፡ « **በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል፡፡ » መዝ. 90 (91) ÷1** ይህንን የተስፋውን ቃል ዘንግተናልና፡፡

## 5.2 <u>የእግዚአብሔር መልአክና ኤልያስ</u>

**« በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፣ እነሆ፣ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ፡፡ በፊቱ ተጠንቀቁ፣ ቃሉንም አድምጡ፤ ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት፡፡ » <u>ዘጸአት 23÷21</u>**

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የሌሎችን መንፈስ ለማርካት ሲል፤ ንጉሡ ብዔልዜቡልን ጠይቁልኝ ብሎ መልዕክተኛ ሰዷል፡፡

**«የእግዚአብሔርም መልአክ ኤልያስን፡- ተነሣ የሰማርያን ንጉሥ መልዕክተኞች ለመገናኘት ውጣና፡- የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ትጠይቁ ዘንድ የምትሄዱት በእስራኤል ዘንድ አምላክ ስለሌለ ነውን? ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ትሞታለህ እንጂ ከወጣህበት አልጋ አትወርድም በላቸው አለው፡፡ ኤልያስም ሄደ፡፡»** ይላል፡፡ እዚህ ላይ ሶስት ግንኙነቶች እናስተውላለን፡፡

አንደኛ እግዚአብሔር ከመልአኩ ተገናኘ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መልአኩ፤ ከኤልያስ ጋር ተገናኘ፤ በመጨረሻም ሶስተኛ ላይ፤ ኤልያስ የአዙሪት ሀሳብና ፍላጎት ከተቀበሉ ሰዎች ጋር ተገናኘ፡፡ በመሆኑም፤ ኤልያስ ከመልዕክተኞች ጋር ሆኖ ወደ አካዚያስ ተመለሰ፡፡ መላዕክተኞቹም፤ ንጉሡ ዘንድ ቀረቡ፡፡





አካዚያስም፤ ለምን ተመለሳችሁ? አላቸው፡፡ እነርሱም አንድ ሰው ሊያገኘን መጣና ሂዱ ወደ ላካችሁ ንጉሥ ተመልሳችሁ፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በሉት፤ **የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ትጠይቁ ዘንድ የምትሄዱት በእስራኤል ዘንድ አምላክ ስለሌለ ነውን? ስለዚህ «ትሞታለህ እንጂ ከወጣህበት አልጋ አትወርድም»** በሉት አለን፡፡ ንጉሡም፤ ይህንስ ቃል የተናገራችሁ ሰው መልኩ ምን ይመስላል? አላቸው፡፡ እነርሱም ሰውዬው ጠጉራም ሆኖ፤ በወገቡም ጠፍር የታጠቀ ነበር አሉት፡፡ እርሱም፤ አሃ!... ቴስብያዊው ኤልያስ መሆን አለበት አለ፡፡ ቀደም ሲል ንጉሡ ኤልያስን ያውቀዋል፡፡

የምናውቀውን ነገር እንዴት ገለል አድርገን፤ ወደ ከፋ አቅጣጫ ውስጥ ገብተን እንደሚሸፈንብን፤ የምንረዳውን ነገር እንዴት እንዳልተረዳነው ሆነን በሕይወታችን ውስጥ ችግሮችን እንደምናበዛና ለሌሎችም ችግር እንደምንፈጥር፤ የአካዚያስ ጉዞ ያሳየናል፡፡

**«በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም፡፡» መዝ. 90 (91) ÷6**

ከዚያ በኋላ ንጉሡ የአምሳ አለቃውን ጠርቶ፤ ከአምሳ ወታደሮች ጋር ወደ ኤልያስ ሰደደ፡፡ ኤልያስም በተራራ ራስ ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡ አምሳ አለቃውም፤ **የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! ንጉሡ ውረድ ይልሃል!** አለው፡፡

እኛ – የምንችለውን ያህል እንታገላለን፡፡ ዕቅዶቻችንና ፕሮግራሞቻችን ውስጥ ሁሉ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ንጉሦች ሁሉ እኛ ከወረድን እናንተም ውረዱ፣ እኛ ከወደቅን እናንተም ውደቁ እያሉ ችግራቸውን ያካፍሉናል እንጂ፤ደስታቸውን አያጋሩንም፡፡

ከተሳካልን እንገፋበታለን፤ ካልተሳካልን ደግሞ እንወድቅበታለን፡፡ ለጊዜው ችግር ስለሌለ የሰማሪያው ንጉሥ፤ የሚያዘውን ኃይል ላከ፡፡ መልዕክተኞቹም፤ በሚገርም ሁኔታ እሺ ብለው ኤልያስን ሊያወርዱ ሄደዋል፡፡

ሞግዚቱም አዝላው ሸሸች፤ ፈጥናም ስትሸሽ ወድቆ ሽባ ሆነ፤ ስሙም **ሜምፌቦስቴ ነበር። ›› 2ኛ ሳሙ. 4÷4**

የፍልስጥኤማውያን ጥቃት ሲበረታ የሳኦል የልጅ ልጅ ማለትም የዮናታን ልጅ ሞግዚት፤ አንድ ሕጻን ተሸክማ ስትሸሽ ሕጻኑ መሬት ላይ ወድቆ ሽባ ይሆናል። ሞግዚቷ ይህንን ሕጻን <u>ሜምፊቦስቴ</u> ብላ ጠራችው። ትርጉምም <u>ወድቆ የተሰበረ ልጅ</u> ማለት ነው።

ሳኦልና ልጆቹ ጊልቦዓ ተራራ ላይ ከቀሩ በኋላ፤ **‹‹ዳዊትም:- ስለ ዮናታን ቸርነት አደርግለት ዘንድ ከሳኦል ቤት አንድ ሰው ቀርቶአልን?›› በማለት ጠየቀ። 2ኛ ሣሙኤል ምዕ. 9÷1**

አንዳንድ ጊዜ፤ ብዙ ሰዎች ስለትልቅነታቸው ይናገራሉ። እኔ እኮ የትልቅ ሰው ዘር ነኝ ይላሉ። የቀኝ አዝማች፤ የግራ አዝማች፤ የፊታውራሪ ዘር የነበርኩ ነኝ! በማለት ይቆጣሉ። ለምንድነው የማልከበረው? ይላሉ፤ ወድቆ ከተሰበረ ምን ዋጋ አለው።

ባለፈው ዘመን የሚፎክሩና በትልቅነት ትዝታ የሚኖሩ፣ ሁሉም ነገር የተሰበረባቸውና ግራ የተጋቡ አሉ። ጊዜ እንዲህ እየተለዋወጠ ሁኔታዎች ተበላሽተው በመካከሉ የተገኘው ትውልድ፤ በትክክል ከታሪኩ ውስጥ ሳይሆን፤ ከጣዖት ውስጥ ተደብቀው የተወለዱ ችግራቸው ብዙ ነው።

አባቶች ባቆዩት በረከት፣ በመሠረቱት ታሪክ ውስጥ እሱ አመለኛና ሉሰኛ ሆነ። አባቶቹ ደክመው ባቆሙት ቢሮ ውስጥ፤ እሱ ሌባና ዘራፊ ሆነ። አባቶቹ በተከሉት፣ በደከሙበት፣ ቀን ከሌሊት ላባቸውንና ወዛቸውን አንጠፍጥፈው ለእውነት የቆሙበትን መንገድ፤ እሱ ነጥቆና ዘርፎ መሸሻ አደረገው። ሲመች እንዲህ ነው! ሲመችን የእግዚአብሔርን መንገድ እንረሳዋለን።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ **‹‹መካን በዘመኑም የማይከናወንለት ሰው ብላችሁ ጻፉ።›› ት/ኤር. 22+30**





## 5.4 <u>ሜምፊቦስቴ የሽሽት ዘመን ልጅ</u>

አሁን ሜምፊቦስቴ መቆም አልቻለም። ወሬው የመጣው ከኢይዝራኤል ነው። **ኢይዝራኤል** ማለት ሰው ይዘራል እግዚአብሔር **ይሰጣል** ማለት ነው ብለናል። ሳኦል ክፋትንና ምቀኝነትን ዘራ፤ ሞትን አጨደ። ሳኦልና ልጆቹ አለቁ!

በዚህ ጊዜ የምታሳድገዋ ሞግዚት ይዛው ስትሸሽ ወድቆ ተሰበረ። ይህ የሽሽት ዘመን ልጅ ነው።

መጀመሪያ ከመሰበሩ በፊት፤ ሽሽት ኑሮው የሆነ ነው። እኛስ እንደዚህ ከመድቀቃችን በፊት፤ ቤተክርስቲያንን አልሸሸንም? ባሕርያችንና ውስጣዊ ሰላማችን በዲያብሎስ ከመናጋቱ በፊት፤ ወላጆቻችን ቤተክርስቲያንን አልሸሹም?

ሜምፊቦስቴ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የሽሽት ዘመን ልጅ ነው። ሽሽት፤ ፍርሃት፣ ጭንቀትና ሰላም ማጣት ነው። ሽሽት፤ በበጎነት ውስጥ ያለመኖር ማለት ነው። በአባቶቹና በአያቶቹ ችግር፤ ይሄ ልጅ እየሸሸ ነው። የአያቱ <u>የአዙሪት መንፈስ</u> ኪሳራ ሆኖ ወደ እርሱ ዞረ።

እናቶቻችንና አባቶቻችን በመንፈሳዊ በረከት የሚኖሩበትን መንገድና ሁኔታ፤ ሊያስተውሉትና ሊገነዘቡት አልቻሉም። በኑሯቸው ውስጥ ክፋትን፣ የጎረቤት ምቀኝነትንና ተራ የሆነ የአካባቢ ኑሮ ጠባያትን ተለማመዱ።

በመጨረሻም ከእግዚአብሔር አምላክ ደጅ ሸሽተው ኑሯቸውን ጀመሩ። ቤተሰብነታቸው በአምልኮት ሽሽት ጎዳና ውስጥ ልጅ ማሳደግ ሆነ።

ስለዚህ፤ **‹‹በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።›› ዘዳግም 5÷9-10**

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ልቦናው ከቤተሰቡ ተከፈለ። ባሕርይው ከቤተሰቡ ወጣ ከአባቱ ፍላጎት፤ ዕቅድና ፕሮግራም ውጭ ሆነ። ሲወጣ ደግሞ ማንንም አላማከረም። በራሱ ጊዜ ተገነጠለ፣ ተለየ፣ የራሱን ሃሳብና መንገድ ፈጠረ። **ትንሹ ልጅ ወዴት እየሄደ ነው?**

አባትየውም ገንዘቡን ለሁለት አካፈላቸው። ከጥቂት ቀን በኋላ ትንሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ በመያዝ፤ ወደ ሩቅ አገር ሄደ።

እኛም፤ ምኞታችን፣ ኑሮአችንና እቅዳችን ይሄ ነው። ወደ ሩቅ አገር መጓዝ። ሁልጊዜ ክብራችን፣ ሞገሳችንና ሃብታችን ያለው ሩቅ አገር ይመስለናል። እዚህማ እንናከሳለን፤ እንባላለን፤ የልቦናችን መሻት፣ የትምህርታችን፤ የእውቀታችን ዳርቻዎች ሁሉ ያሉት፤ ሩቅ አገር ነው። ሩቅ፣ በጣም ሩቅ።

ታላቅየው ከነሀብቱ ያለው አባቱ ጋር ነው። ምክንያቱም፤ ትልቁ ልጅ፤ የአባቱ መንከራተትና በኑሮ የመጎሳቆል ደረጃውና በሕይወቱ ታሪክ ውስጥ ያለውን ሂደት በቅርብ ስለሚከታተል በአባቱ ድካም ውስጥም እርሱ ስለነበረበት የድካሙ ተካፋይ ከመሆኑም ጋር የሚሰማው ስሜት ከትንሹ ልጅ እጅግ የተለየ ነው። ምክንያቱም፤ በታሪክ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ የኑሮ ደረጃዎችና ጊዜ፣ ዘመን የሚያመጣውን ጉዳት አይቶና ኖሮበት ማለፍን የሚያህል አስተማሪ ያገኘ ስለሆነ ነው። ትንሹ ልጅ ግን፤ ወቅቱና ሰዓቱ ከአባቱ ድካም በኋላ የመጣው ኑሮና ጊዜ ያለው ሰላምና ክብር፣ ጠላት የሌለበት ሀብትና ትርፍ፣ ብዙ ሰው የሚመለከተው ግርማና ሞገስ የተቀባይነት ፍቅር፣ ሰፋ ባለ የማሕበራዊ ግንኙነት ዘርፍ፣ የተረጋጋ ወቅት ላይ በመድረሱና ለተተኪው ትውልድ ለሚያወርሰው ጉዳይ ባለውና የነበረውን በማቆየት ዕቅድ መካከል ትንሹ ልጅ ተገኘ።

በችግርና በመከራ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚጠብቅላቸው፣ መንፈሳዊ በረከታቸውን የሚይዝላቸው ኃይል እንዳለ ያምናሉ።



በማለዳ መያ'ዝ

ትንሹ ልጅ፤ ሀሳብ ሲያፈልቅ ከትልቁ ልጅ በልጧል። በተደማጭነት በኩልም አባቱ በፍቅር ያየው ስለነበር፤ አባቱ ገንዘቡን አካፈለው እንጂ፤ ወዴት ትሄዳለህ? የት ትኖራለህ? የትስ ትደርሳለህ? ዕቅድህስ ምንድነው? ለማለት አልቻለም። የሚወደው የትንሹ ልጅ ጉዳይ፤ ብዙ ነገሮችን ደብቆበታል።

እኛም፤ ባሕልና ሃይማኖት ተደባልቆብን፤ መሠረታዊ የእምነት መንፈሳዊ ምሪት ወደ ክርስቶስ የጸጋ ሙላት የሚያቀርበንን ታሪካዊ የሕይወት ጉዞ እያቃለልን በመመልከት፤ በክፉ መናፍስት ሥውር የምስጢር ጥቃት ውስጥ በመግባት፤ ትውልዳችን የሚቆምበትን መንፈሳዊ የእምነት ደረጃ ልናስጨብጠው ካለመቻል ጋር የገጠመን ችግር፤ ጊዜ፣ ዘመን፣ ዓለማዊ ፍልስፍናና፣ እውቀት የሚፈታው ሆኖ አልተገኘም።

ስለዚህ በመናፍስት አደጋ ውስጥ፤ ለመግባት ባሕሎቻችን ተመቻችተዋል። አሁን ቅድሚያ የምንሰጠው ለእምነታችን ሳይሆን፤ ለባሕላዊ ወጎቻችን ነው። እነዚህ የባሕልና የልማድ እሴቶቻችን ደግሞ፤ በተወራራሽነት በብዙ መልኩ ከክፉ መናፍስት ጋር የተሳሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

አብዛኛዎቹ የጠላትን ኃይል የሚያዳብሩ፣ የክፉ መናፍስቱ አካሄዶች ባሉበት ገበና ውስጥ ነው የተወለዱት። ይህ ምንም ጥርጥር የለውም። ቢያንስ እናታችን ወይም አባታችን በጨሌ ውስጥ አልፈዋል። ወይም ቅድመ አያቶቻችን ፍጹም ከአጋንንት አምልኮ ጋር በተያያዘ ዕድሜና ዘመናቸውን ጨርሰዋል።

ስለዚህ ትንሹ ልጅ በእኛም ዘመን ሂደት ውስጥ በየትኛውም አኗኗራችን ውስጥ እናገኘዋለን። እኛ ትናንሾቹ ታዲያ አሁን ብዙ ነገር ሊባክንብን ነው። የሕይወት፣ የገንዘብ፣ የአእምሮ፣ የልቦና፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር፣ ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የመጣ የበረከት ገንዘብ፤ እነኚህ ሁሉ በባከኑበት ዓለም ላይ ነው የምንገኘው።

